**ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ**

# ትግሉ ተጀመረ!

ህወሃት/ኢህአዴግ የዴሞክራሲና የህግ የበላይነት ጥያቄ ሲቀርብለት ዘወትር የሚያሳው መቃብሩን ነው። የአንድነት ጥያቄ ሲቀርብ ምላሹ "እኛ ከፈለሰፍነው አንድነት ውጭ ሌላው አንድነት በኢህአዴግ መቃብር ላይ ካልሆነ በስተቀር የማይታሰብ ነው" የሚል ነው። የመሬት ባለቤትነት ጥያቄ ሲነሳ "የመሬት ባለቤትነት ጥያቄ ህያው የሚሆነው በኢህአዴግ መቃብር ላይ ብቻ ነው" በማለት ወደ መቃብሩ ያመላክተናል። አንቀፅ 39 በታኝ መሆኑን ህዝብ ሲገልፅ "የህዝብ ልጆች የተሰውለት የትግሉ የማዕዘን ድንጋይ ነው፣ እኔ ካልሞትኩ በስተቀር" በማለት ለክቡር አላማ የተሰው ሰማዕታት አፅም ላይ ቆሞ ይዘምራል። ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት ናት፣ ላንተም ቢሆን የባህር በር ያስፈልግሃል ሲባል "ሞቼ ነው ቆሜ ኢትዮጵያ የባህር በር የሚኖራት" እያለ በማቅራራት መቃብሩን ያሳየናል።

የትምህርት ፖሊሲው አዲሱን ትውልድ እየበላው ነው ተብሎ ማሻሻያ እንዲያደርግ ሲለመን "የፍየል ወጠጤ" እያለ ይፎክራል፤ መቃብር ያሳየናል። የግብርና ፖሊሲው ስህተት በመሆኑ ይታረም ሲባል "እህል ኤክስፖርት ማድረግ ጀምሬያለሁ፣ የአርሶ አደሩ ህይወት ተለውጧል። እኔ ከሞትኩ አርሶ አደሩ ይራባል፣ ይጎዳል፣ እኔ ለገበሬው ተፈጥሬያለሁ። እኔ ከሞትኩ…" እያለ መቃብር ያሳየናል። በኢኮኖሚው መስክም ሲመከር "ሁለት ዲጂት እድገት አሳይቻለሁ። እኔ ከሌለሁ…" በማለት ወደ መቃብሩ ይጠቁመናል። በምርጫ ተሸንፈሃል ሲባል ‹‹ኢንተርሐምዌ›› የርስ በርስ ጭፍጭፍ እያሳየ እኔ ከሌለሁ በማለት ትልቁን መቃብር ያመላክተናል። በጥቅሉ ኢህአዴግ መቃብርና ጉድጓድ ያላሳየበት ጊዜ የለም። ለውጡ የመቃብሩ መጠሪያ መቀየሩ ነው። ድሮ ኢህአዴግ ነበር አሁን አቶ መለስ ወይም የአቶ መለስ መቃብር ተብሎ መተካቱ ነው።

ከላይ በዘረዘርናቸው ጉዳዮችም ሆነ በሌሎች መስኮች ህወሃት/ኢህአዴግ ምክርና ተግሳፅ ሲሰጠው ከመቀበል ይልቅ "እኔ ከሌለሁ" በሚል መቃብሩን እያሳየ አገርም ህዘብም ክፉኛ እየተጎዱ ነው። መቃብር እያየን መቃብር ውስጥ እየገባን ነው። በርካታ አስተያየት ሰጪዎች እንደሚሉት "ፈሪ መንግስት ዘወትር የሚታየው መቃብር ነው። የሚማማለውም በመቃብር ነው" በህወሃት/ኢህአዴግ ጥላ ተለክተው የተሰሩት ልጥፍ ፓርቲዎችም መቃብራቸውን እያዩ አገር፣ ልጅ ልጆቻቸው፣ እነሱም የቁም ሞት እየሞቱ ነው። ግን እስከመቼ? የሚገርመው "እኔ በህይወት እያለሁ ለውጥም ሆነ መሻሻል አይታሰብም በማለት ስልጣን በያዘ ማግስት መቃብር ማሳየት የጀመረው ህወሃት/ኢህአዴግ እሱ ባስቀመጠው የጫዋታ ህግ መሰረት ወደ ሚመኘው መቃብሩ ሊሸኙት የተነሱትን የህዝብ ልጆች የፈጠራ ወንጀልና መረጃ እየሰበሰበ፣ በፈጠራ ክስ፣ ራሱ ፈራጅ ሆኖ ለስቃይ እየዳረገ መሆኑ ነው። ለመነሻ ይህን ካልን ወደ ዋናው የመግለጫችን ርዕስ እናምራ!

ዘወትር መቃብሩን እያሳየ የሚምለው ህወሃት/ኢህአዴግ፣ ባለፉት 20 ዓመታት የስልጣን ዘመኑ "የሹም ዶሮ ነኝ…" እንዲሉ አገሪቱንና ህዝቦቿን ወደ መቃብር ከሚወረውር የአፈና ርምጃው ከማፈግፈግ ይልቅ ወደ መቃብሩ በፍጥነት እየተንደረደረ መሆኑን የሚያረጋግጡ ተግባራት ማከናወኑን ገፍቶበታል። እስር፣ ስቃየመከራ፣ የጅምላ ግድያ፣ የመብት ረገጣና ንጹሃን ዜጎችን ማሳደዱ ተጠናክሮ ቀጥሏል። አስገድዶ መድፈር፣ የአገር ንብረት ማሸሽ፣ ህፃናትን መሸጥ፣… በተግባርየምናየውናየምንሰማውምፈር የለቀቀ የአምባገነናዊ ስርአትመገለጫ የሆኑትንግብሮች ነው።

ህወሃት/ኢህአዴግ የኢትዮጵያ ህዝብ ለመብቱና ለነፃነቱ ቀንዓዊ ከመሆኑም ባሻገር እነዚህ የህልውናው መሰረት የሆኑ ዕሴቶች ተጠብቀውና ተከብረው እንዲኖሩ ደረጃ በደረጃ መወሰድ የሚገባውን እርምጃ ጠንቅቆ የሚያውቅ መሆኑን የዘነጋ ይመስላል። የህዝቡን መብት ለማስከበር በቡድንም ሆነ በተናጠል ጥያቄ የሚያነሳ ኃይል ብቅ ሲል ህወሃት/ኢህአዴግ የማጥፊያ ሰይፉን

መዝዞ "ሕገ መንግሥቱን ሊንዱ"፤ "የህዝቡን ሰላም ሊያደፈርሱ"፤ "ሽብር ሊነዙ"... ወዘተ እያለ ሲያስፈራራ፣ ሲያስር፣ ሲገድል፣ ሲያሳድድ ይታያል። ህወሃት/ኢህአዴግ ማስፈራሪያ የሚያደርገው ሕገ መንግስት የህዝብ መብት ማስከበሪያ፣ ነፃነት ማስጠበቂያ መሣሪያ ሆኖ ካላገለገለ እሱ በጀመረው የ"አስቀድማችሁ ቅበሩኝ" ጥሪ መሰረት መፍረሱ አይቀሬ መሆኑን የዘነጋው ይመስላል።

ያ! የሚፈራው የህዝቦች ንቅናቄ አፍጥጦ ሲመጣበት ቀደም ሲል ጀምሮ የኖረበትን የአደገኛ አሸባሪነት ባህሪውን ይፋ ያወጣው ራሱ ህወሃት/ኢህአዴግ ነው። እውነትን በመፃፋቸው መዓት እንዳመጡ አድርጎ ያሰራቸው ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ እና አምደኛ ርዕዮት ዓለሙ የህወሃት/ ኢህአዴግ ውስጣዊ ርደት የፈጠረው የድንጋጤ ዕብደት ሰለባዎች ናቸው። "መቼ ነው መከራ የምታቆሙት? መቼ ነው ማሰቃየት የምታቆሙት? መቼ ነው ከኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ የምትወርዱት፣ ህዝብ ጠልቷችኋል፣ መሮታል፣ አይፈልጋችሁም" በማለት ባደባባይ የጠየቁትንና ኢህአዴግ ከፓርቲ አምባገነንነት ወደ ግለሰብ አምባገነንነት ተለውጦ፣ አባላቱ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ዙፋን ከማስጠበቅና እሳቸው የተናገሩትን እንደበቀቀን ከማስተጋባት የዘለለ ስራ እንደሌላቸው የተናገሩትን የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ምክትል ፕሬዝዳንት አቶ አንዱዓለም አራጌ፣ እዉቁ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፣ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ብሄራዊ ምክር ቤት አባላት አቶ አሳምነው ብርሃኑ እና አቶ ናትናዔል መኮንን፣ የመላው ኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ አባል ዘመኑ ሞላ፣ አንጋፋው የኪነት ባለሞያው የሆኑት አርቲስት ደበበ እሸቱ፣ የኦሮሞ ሕዝብ ኮንግረስ አመራር የሆኑት አቶ ኦልባና ሌሊሣ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህር የሆኑትና የኦሮሞ ፌደራላዊ ዴሞክራስያዊ ንቅናቄ ምክትል ሊቀ መንበር በቀለ ገርባ የሚመሩት ትግል ህዝባዊ መሆኑን እና ከኋላቸው ያሰለፉትን ኃይል ከቶውንም ሊቋቋመው እንደማይችል ያወቀው ህወሃት/ኢህአዴግ መሪዎቹንና ቀላጤዎቹን አስሮ በሀሰተኛ ክስ "አሸባሪ ናችሁ" ማለቱ የጭንቀቱ ጉልህ ማሳያ ነው።

የወገኖቻችንን እስር አምርረን የምንቃወምና ከእስር እንዲለቀቁ የበኩላችንን የምናደርግ ቢሆንም፣ ቀደም ሲል የሰብዓዊ መብት ጥበቃው ድርጅት (Human Rights Watch)፣ ቢቢሲ፣ በቅርቡ ደግሞ ዊኪሊክስ (ሹልክዓምድ) ይፋ ያደረገው የስርዓቱ ገመና፣ ህወሃት/ኢህአዴግ አባላት ንጹሃንን አጉረው ከሚያሰቃዩበት ከማዕከላዊ እስርቤት ማዕከል ሰራተኞች የወጣው የእማዋይሽ አለሙና ሌሎች ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችን ላይ የሚፈፀመው ግፍ ምስክርነት እንደሚያስረዳውና እኛም ባለን መረጃ በእስር ቤት የሚፈፀመው አውጫጪኝ የሰብአዊ መብትን የሚጥስ፣ ርህራሄ የጎደለው በመሆኑ የዜጎቻችን ደህንነት በእጅጉ ያሰጋናል።

በአንድ ጀንበር ህግ እያዘጋጀ፣ በህግና በአዋጅ ስር ተጠልሎ ወገኖቻችንን እያሰረና እያሰቃየ ያለው የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ አንዳንድ ባለስልጣኖቹ በተስፋ መቁረጥና በልዩ ጥበቃ ስር መሆናቸው የሚታወቅ ቢሆንም ስርዓቱን በመቃወም ሊከፍሉት የሚገባውን ዋጋ አልከፈሉምና እየሞተ ካለው ስርዓት ጋር አብረው ከመጠየቅ እራሳቸውን እንዲያድኑ አበክረን እንጠይቃቸዋለን። ከታሪክና ከዓለም የቅርብ ቀናት እውነታ እንዲማሩም ወገናዊ ጥሪ እናቀርባለን።

አገሩን የሚጠብቅ፣ ህዝብን የሚያከብር፣ ለህግና ለስርዓት የሚገዛ፣ የአገሪቱን ሃብት በአግባቡ የሚንከባከብ፣ ለዲሞክራሲ መብቶች ተግቶ የሚሰራ፣ በህግ የበላይነት የሚያምን መንግስት እየናፈቀን ስንት ትውልድ አለፈ። ህዝብ "አንቱ" የሚለው መንግስት እየተመኘ ስንት ዘመን ቆጠርን? ህዝብ "በቃ" ሲል "አሜን" ብሎ የሚቀበል አገልጋይ መሪ እንደተመኘን ይኸው አለን። የምንመኘውና የገጠመን ተለያይቶ አገርም፣ ህዝብም እየማቀቁ ነው። መገለጫው ፀረ ኢትዮጵያዊነት፣ ፀረ ህዝብነት፣ ፀረ አንድነት፣ ፀረ ዴሞክራሲ፣ ፀረ ፕሬስ፣ ህዝብ ለሚፈልገው ሁሉ ፀር የሆነ ስርዓት እስከመቼስ በኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ ይቀመጣል?

ይህ ፀረ ኢትዮጵያ ስርዓት የመንግስትነት ጠረኑ የጠፋ ለመሆኑ ምልክት እየታየ ነው። ዛሬ ባገራችን ህገወጥነት ነግሷል። ዛሬ ባገራችን ህግ ከጥቅም ውጪ ሆኗል። ዝርፊያና አስገድዶ መድፈር ይፈፀማል። ባለስልጣናት ገንዘብ ያሸሻሉ። እስርና ስቃይ ይበዛል። የሚፈሩ ተቃዋሚዎች ይታደናሉ። በርካታ ማጎሪያዎች ይከፈታሉ። የጦር መሳሪያ ሽመታ ይጧጧፋል። የፋይናንስ ፍሰት ይናጋል። ስራ አጥነትና ዝርፊያ ይስፋፋል። የሚበሉና የማይበሉ ህዝቦች መተያየት ይጀምራሉ ወዘተ፤ እንግዲህ ባገራችን ያልታየው የቱ ነው? ከያቅጣጫው የሚወጡት ሪፖርቶች ሁሉ የሚያረጋግጡልን ይህንኑ እውነት ነው።

የዚህ ሁሉ ድምር መጨረሻው ጥፋት ብቻ ነው። ህወሃት/ኢህአዴግ ዓላማው ጥፋት ቢሆንም ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ጥፋት ሳይከተል ከጎሳ ይልቅ ለሰብአዊነት ቅድሚያ እንስጥ በሚለው የፕሮግራሙ መሰረታዊ መርህ መሰረት መቃብራችንና መቃብራቸውን ከሚያሳዩን አምባገነኖች ኢትዮጵያን የማላቀቁ ሂደት ከመቼውም በበለጠ በቅንጅት እንዲቀጥል ጥሪውን ያቀርባል። ተሳታፊነቱንም ያረጋግጣል።

በሌላም በኩል በሊቢያ አምባገን መሪ ልጅ ቤት በሞግዚትነት እየሰራች የፈላ ውሃ ተደፍቶባት ለከፋ አደጋ የተዳረገችው እህታችን ሸዋዬ ጉዳይ ለተራ የፖለቲካ ገበያ ለማዋል የሚደረገውን እንቅስቃሴ ሁሉ አጥብቀን እንኮንናለን። የሸዋዬ የሌሎች ኢትዮጵያውያን ስደት ያገሪቱ ፖለቲካና የአቶ መለስ እኔ ብቻ አውቃለሁ ፖሊሲ ውጤት ነውና ህወሃት/ኢህአዴግ ለሸዋዬ ተሚጋች የመሆን ሞራሉም ሆነ ውክልናው እንደሌለው የራሱ ታሪክ ቋሚ ምስክር ነው።

እህታችን የደረሰባት አጥንት ዘልቆ የሚገባ ህመምና ስቃይ እያቃጠለን ሌሎችስ ብለን ለመጠየቅ እንገደዳለን። ”ድረሱልን” ሲሉ የነበሩ ዜጎች የት ደረሱ? ስንቱ አገራቸው ገቡ? ስንቶች ሞቱ? ስንቶች የባህር ሲሳይ ሆኑ? ለህዝቡ የሚጨነቅ መንግሥት የሚመልሰው ጥያቄ ነውና በሊቢያ ስለነበሩት ዜጎቻችን ለሸዋዬ ብቻ አልቅሰን ሌሎችን በሃሳብ ቀብረን ዝም የምንለው አይሆንም። በተለያዩ አረብ አገራት ብዙ ሸዋዬዎች ግፍ ደርሶባቸዋል። በርካቶች ተከራካሪ በማጣት ከነስቃያቸው አልፈዋል. . .መገለጫችን በሆነው ስደት ጉዳይ ብዙ ብዙ ጣጣ አለ! ከፎቅ ላይ የተወረወሩ፣ በእሳት የተቃጠሉ፣ በተለያዩ እስር ቤቶች የተጣሉ፣ ጤናቸው የታወከ፣ ለቤተሰቤ ምንም ሳላደረግ በሚል ካገር እንደወጡ የጠፉ፣ አሁን ደግሞ እሳት በሚነድባቸው በየመንና በሶሪያ ያሉት ወገኖቻችን ጉዳይ እረፍት የሚነሳ ነውና አገር ወዳዶች የችግሩ ሰንኮፍ ላይ ማተኮር ግድ ይለናል።

በመግቢያው ላይ እንደተጠቆመው ህወሃት/ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ለውጥ የሚመጣው በመቃብሩ ላይ ብቻ እንደሆነ በመግለጽ በሰላማዊ ትግልና በሰላማዊ ታጋዮች ላይ ጦርነት ያወጀው ከዛሬ 20 ዓመት በፊት ነው። ከ20 ዓመት በፊት በልዩነት እንደማያምን አስረግጦ የተናገረው ህወሃት/ኢህአዴግ በመረጠው መንገድ ወደመቃብሩ ሲገፋ ‹‹ብቻየን ለምን›› በሚል ውድ የኢትዮጵያ ልጆች ላይ እየፈፀመ ያለው ዘግናኝ ስቃይ፣ በአገራችን ላይ የወደቀው መከራ እንዲወገድ ይበልጥ የሚያነሳሳ እንጂ ትግሉን የሚያራዝም አይሆንም!! **እንዲያውም ትግሉ ተጀመረ እንጂ**!

## ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ

***************************************************************************************************

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ ዋና ዳይሬክተሩን ለአቶ ኦባንግ ሜቶ (obang@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡*

